2. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ያለው ስለሆነ የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 20465

ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሃመድ
አሰግድ ጋሻው
ሂሩት መለሠ
ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች**……….. አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ ጠበቃ ጉሣዬ ጉርሙ ቀረቡ

**መልስ ሰጪ**……. ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥረ ነገር ሥልጣንን በሚመለከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁኑ መልስ ሰጭ ፀሐይ ዮሐንስ በህፃን ተመስገን ቱጂ ላይ በደረሰው የአካል ጉዳት ምክንያት በጉዳት አድራሹ እና ጉዳት ባደረሰው ንብረት ባለቤት ላይ የካሣ ጥያቄ (ክስ) አቅርበዋል፡፡ ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በተነሳው የካሣ ክርክር የአሁኑ አመልካች ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የተከራካሪ ወገኖችን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ ተከሣሾችንም ሆነ ጣልቃ ገቡን ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ጠቅሶ ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝን አቤቱታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ የአሁን አመልካችና መልስ ሰጪን ካከራከረ በኋላ፡-

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችለው የስረ ነገር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ መስርቷል ይህንንም አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚከተሉትን ምክንያቶች አስፍሯል፡፡

ይግባኝ ባይ የይግባኝ አቤቱታውን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊያቀርብ የቻለው ይግባኝ ባዩ በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት መሆኑን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይግባኝ ባይ በሁለት የአንድ ክልል ነዋሪዎች መካከል በተነሳ የፍትሐብሔር ክርክር ላይ ጉዳት ላደረሰው መኪና የመድን ሽፋን በመሰጠቱ የተነሳ ጉዳት አድርሷል በተባለው መኪና ባለቤት እግር ተተክቶ ጣልቃ ገብቶ ከመከራከሩ በስተቀር የራሱን መብትና ግዴታ በሚመለከት የቀረበበት ክስ አልነበረም፡፡ በስር ፍ/ቤትም የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልከቶ ያነሳው ክርክር አልነበረም፡፡ ስለሆነም ክሱ የፌዴራል ጉዳይን የሚመለከት ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ለመወሰን የሚያስችለው ስልጣን የለውም፡፡ ስለሆነ በፍ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(2) መሠረት ውሣኔውን አጽንተን ይግባኙን ሰርዘናል በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይኸው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ነጥብ በመንቀስ እንዲታረምለት ነው፡፡ ነጥቦቹም፡-

- ሥልጣንን አስመልክቶ በተከራካሪ ወገን ክርክር ሳይነሳ ፍ/ቤቱ በእርሱ አነሳሽነት ማንሳቱ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን ያሳያል፡፡
- የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ውሣኔ የሰጠው ክርክሩ ከያዘው የገንዘብ መጠን አንፃር በህገ-መንግሥቱ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን በመተካት ስለሆነ እንጂ ጉዳዩ የፌዴራል ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ውሣኔ እንዲሰጥ አዋጅ ቁጥር 322/95 ስለሚከለክለው የይግባኝ አቤቱታው ለፌዴራል ከፍተኛ



ፍ/ቤት መቅረቡ ስነ-ሥርዓታዊ ሆኖ እያለ ውድቅ መደረጉ ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም የሚሉት ናቸው፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ክሱም ሆነ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን፣ ይግባኙን ተመልክቶ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችለው የሥረ -ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ ለሌላው ተከራካሪ ወገን ስለዚሁ ጉዳይ ክርክር ባይቀርብበትም ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት አንስቶ መዝገቡን መዝጋት የሚችል ስለመሆኑ በሥነ-ሥርዐት ህጉ በአንቀጽ 9፣231፣207፣211 እና 228 የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ረገድ ይህ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበው/ በማለት የቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ 2ኛውን ነጥብ በሚመለከት በመጀመሪያ ክርክሩ የተነሣው የክልሉ ነዋሪ በሆኑ ሁለት ግለሰቦች መካከል ነው፡፡ በዚህ ክርክር አመልካች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተፈቅዶለታል፡፡ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በተፈቀደለት ጊዜ ጣልቃ ገቢው በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ምክንያት ብቻ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር እንዲወድቅ ሊያደርገው ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ አመልካች የይግባኙ ጉዳይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ ይገባዋል ለሚለው አቤቱታው መሠረት ያደረገው የከፍተኛ ፍ/ቤትን ስለማደራጀት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 322/95ን በመጥቀስ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ ይዘት እንደሚያስረዳው ክርክር የተነሣበትን የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልን ጨምሮ በ5ቱም ክልሎች የሚገኙ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ቀደም ሲል በፌዴራል ጉዳይ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/2 በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሰረት ስለከፍተኛ ፍ/ቤት ሆነው በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣናቸው ጉዳዮችን ተቀብለው ለማየትና ለማስተናገድ ተሰጥቷቸው የነበረው ሥልጣን ቀሪ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ የነዚህ ክልሎች ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩትን የፌዴራል ጉዳይ በይግባኝ ተቀብለው ለማየት ያላቸውን ሥልጣን ያስቀረ

አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚያግደው ምክንያት አልነበረም፡፡ እራሱ ባነሳው የክርክር መስመርም ቢሆን ይህንኑ ለመንቀስ ታስቦ እንጂ ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በይዘቱ የፌዴራል ጉዳይ ነው ለማለት ተፈልጎ አይደለም፡፡

ስለሆነም ሥልጣንን አስመልክቶ የፌዴራል ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ተወስኖ ነገሩን ሰምቼ ለመወሰን የሚያስችለኝ ሥልጣን የለኝም በሚለው ውሣኔ መገደብ ሲገባው ከዚህ አልፎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንተን ይግባኙን ሠርዘናል ማለቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**ው ሳ ኔ**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.ቁ.38232 ግንቦት 18 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡ ከዚህ በፊት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 21270

ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
ሒሩት መለሠ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ ወይንሸት አበራ በሌለችበት የሚታይ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የዕግድ ይነሳልኝ ጉዳይ አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ ሆነው በወ/ሮ አስናቀች ቶሎሣ ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ የዚህም ክስ ውጤት እስከታወቀ ድረስ የተከሳሽ የወ/ሮ አስናቀች የሆነው ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ታግዶ ይቆይ ዘንድ ክሱ በቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 መሠረት የዕግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡

አመልካችም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለወ/ሮ አስናቀኝ ቶሎሣ በሰጠው የብድር ገንዘብ ምክንያት ይህንኑ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ንብረት አስቀድሞ በመያዣ የያዘው መሆኑንና የብድር ገንዘቡ እንደ ውሉ ባለመመለሱ፤ ተበዳሪ ዕዳውን ለመክፈል ባለመቻሏ ምክያት በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንኑ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ለመሸጥ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ከላይ በተገለፀው አኳኋን በፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆኑን በመረዳቱ አስቀድሞ በመያዣ የያዘው መሆኑን